*In the loving memory of*

# MEQUANINT GEZU



## ኣቶ መኳንንት ገዙ

1957-2013

በአቶ መኳንንት ገዙ ድንገተኛ ሞት የተሰማንን ሀዘን እንገልፃለን

አብሮ አደግ ጔደኞቹ፡
ከቤተሰብ አባላቶች
ከልጆቹ ጔደኞቹ፡
ከ27 ዕድር አባላቶች

FUNERAL AND PRAYER SERVICE
9902 Braddock Rd, Fairfax, Virginia
22032

## የአቶ መኳንንት ገዙ አጭር የህይዎት ታሪክ

አቶ መኳንንት ገዙ በ1957 ዓ.ም በበጌምድርና ስሜን ክፍለ ሀገር በጎንደር ከተማ ቀሃ እየሱስ ከአባታቸዉ ከአቶ ገዙ ደስታና ከእናታቸዉ ከወይ/ይጋርዱ አራጋዉ ተወለዱ።

ዕድሜዉ ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በመሰረተ ትምህርት ቤትና ሁለተኛ ደረጃ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማጠናቃቅ ላይ እያለ በጊዜዉ የአገሪቱ የፖለቲካ ለዉጥ ምክንያት በ1975ዓ.ም በእድገት በህብረት የዕዉቀትና የሥራ ዘመቻ በመሳተፍ ለሚወደዉ አገርና ለሚያከብረዉ ሕዝብ አስተዋፅዖ በማድረግ ግዴታዉን ተወጥተዋል።

አቶ መኳንንት ከእድገት በሕብረት ዘመቻ ከተመለሰ በኋላ የግል ጥቅም ሳያታልለዉና በጊዜዉ መሳተፍ የነበረበትን ከፍተኛ የትምህርት ዕድል በመተዉ ለሃገሬና ለህዝቤ እታገላለሁ ሁሉም ነፃ ካልወጣ በማለት በ1977 ዓ.ም በሓምሌ ወር ከኣጋር ጓዶች ጋር የኢትዮጵያ ህዝብ ኣብዮታዊ ፓርቲን በመቀላቀል ወደ በረሃ በመዉጣት ለተወሰኑ ዓመታት በተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች በመዘዋወር የፖለቲካ ንቃትና ትምህርት ሲያስተምር ከቆዩ በኋላ በጊዜዉ በአካባቢዉ ይንቀሳቀስ ከነበረዉ የኢሕኣፓ የትጥቅ ትግል ክንፍ (ኢሕኣሠን) ሠራዊት በመቀላቀል በተለያየ የድርጅቱ የትግል ሥልቶች በመሳተፍ ይህ ነዉ የማይባል ጀግንነት በማሳየት ከኣጋር ጓዶቹ ጋር ተሳትፈዋል።

አቶ መኳንንት እንደ ኣዉሮፓዊያን ኣቆጣጠር በ1979 ዓ.ም ወደ ሱዳን በመሄድ ለአንድ ዓመት ከቆየ በኋላ 1981 ዓ.ም ወደ ኣሜሪካን ኣገር ሂዩስተን ቴክሳስ በመምጣት ያ ቅድሚያ ለትግሉ ነዉ ብሎ ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል ትምህርት ቤት በመግባት በመከታተል ላይ እያለ ኣሁንም እንደተለመደዉ "መጀመሪያ ቤተሰቤን መርዳትና ኑሮዋቸዉን ማሻሻል" በሚል መርህ ትምህርቱን ኣቋርጦ በተለያየ የሥራ ሞያ በመሰማራት ቤተሰቡን የረዳ እህት ወንድሞቻቸዉን ያሥተማረና ለቁምነገር ያበቃ ወንድም ነበር ።

አቶ መኳንንት በሂዩስተን ቴክሳስ በሚኖርበት ወቅት ከዉድ ባለቤቱ ከውይ/ሓርግ ከበደ ጋር በመተዋወቅ ለተወሰነ ጊዜ ኣብረዉ ከኖሩ በኋላ ወደ ቨርጂኒያ ስቴት በመምጣት ትዳር መስርተዉ ሶስት ልጆችን በጋራ አፍርተዋል ።

አቶ መኳንንት በዋሽንግተን ዲሲ የተለያዩ የመረዳጃ ማህበራትን በመመሠረትና በመምራት ከፍተኛ አስትዋጽዖ ኣድርጓል ከዚሁም ትልቁን ቦታ የያዘዉ የጎንደር ልማትና ህብረት ድርጅት ነዉ እንዲሁም ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በሞያ ዘርፍ የተደራጀዉን ኣላይድ የታክሲ ኩባንያ ግንባር ቀደም በመሆን በከፍተኛ ጥረት እንዲቋቋምና ለእድግቱም ይህ ነዉ የማይባል አስተዋፅዖ ኣድርጓል ።

አቶ መኳንንት ለተቸገረ ደራሽ ለተራበ አጉራሽ ሰዉ በልቶ የሚጠግብ የማይመስለዉ ሰለቸኝ ሳይል ዘመድ ኣዝማድ ሰብሳቢ መካሪና ተቆርቋሪ ለቤተሰብ ችግር በግንባር ቀደም የሚገኝ የታመመ ጠያቂና አስታማሚ ነበር ።

አቶ መኳንንት በኣደረበት ህመም በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ግንቦት 30 2013 ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየን።

ለባለቤቱ ለወ/ሮ ሓረግ ከበደ ለልጆቻቸዉ ለሩፋኤል መኳንንት፡ለዳግማዊ መኳንንት፡ለልሳኑ መኳንንትና እንዲሁም ለመላ ቤተሰባቸዉና ለወዳጅ ጓደኞቻቸዉ ቸሩ እግዚአብሔር ብርታትንና መጽናናትን ይስጥ ።

**ኣሜን**